# "በትራንስፖርት ባለስልጣን"

# አገር አቀፍ የንግድ ተሽከርካሪዎች

# የኪራይ ትራንስፖርት ደረጃ እና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ

# ቁጥር 886/2013

የትራንስፖርት ባለስልጣን
አዲስ አበባ
የሰርቲፊኬሽን አገልግሎት

መጋቢት 2011 ዓ.ም

## መግቢያ

የንግድ ተሽከርካሪዎች የኪራይ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚንቀሳቀሱት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በመሆኑ አሠራራቸውን እና አደረጃጀታቸውን ወጥና አገራዊ ይዘት እንዲኖራቸው በማድረግ፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ፍትሃዊና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሆን በማስቻል እና ተጠያቂነትን በማረጋገጥ በውድድር ላይ የተመሠረተ አሠራር እንዲኖር ለማድረግ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የትራንስፖርት ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 468/1997 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 1 (ረ) መንገደኞች፣ ዕቃዎች፣ ፖስታዎች በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማዉጣትና አፈጻጸሙን መከታተል በተሰጠው ሥልጣን እና ተግባር መሰረት ይህንን አገር አቀፍ የንግድ ተሽከርካሪዎች የኪራይ ትራንስፖርት ደረጃ እና አገልግሎት አሠጣጥ መመሪያ አዉጥቷዋል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "አገር አቀፍ የንግድ የተሽከርካሪዎች የኪራይ ትራንስፖርት ደረጃ እና አገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 686/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) "ባለስልጣን" ማለት በፌዴራል ደረጃ የመንገድ ትራንስፖርትን ለመምራት ሕጋዊ ሰዉነት ያገኘው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ነው።
2) ."አግባብነት ያለው አካል" ማለት የመንገድ ትራንስፖርትን ለመምራት ስልጣን የተሰጠው የክልል ወይም የከተማ ትራንስፖርት ቢሮ ነዉ።
3) "አዋጅ" ማለት ማለት የትራንስፖርት አዋጅ ቁጥር 468/1997 ነው።



የትራንስፖርት ባለሥልጣን

4) "**ኦፕሬተር**" ማለት በንግድ ተሽከርካሪ የኪራይ አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረት ወይም ድርጅት ወይም ሠራተኛን ነው ።

5) "**የብቃት ማረጋገጫ**"ማለት በአዋጁ መሠረት በንግድ ተሽከርካሪ የኪራይ አገልግሎት ላይ ለሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች አከራይ ማኅበራት ወይም ድርጅቶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ነው።

6) "**ውድድር**" ማለት በማህበራት ወይም በድርጅቶች መካከልና ከአንድ ማሕበር ወይም ድርጅት በላይ የሆኑ አገልግሎት ሰጭዎች በሚሰጡት ፍትሐዊ የአገልግሎት ዓይነት ዋጋን፣ ምቾትን እና የደኅንነት መሣሪያዎችን መሠረት በማድረግ ተገልጋዩ የራሱን ምርጫ በመወሰን የሚገለገልበት አፈፃፀምና የተሽከርካሪ ኪራይ አቅርቦት ሥርዓት ነው።

7) "**ክልል**" ማለት በህገ መንግስቱ አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ያካትታል።

8) "**ተቆጣጣሪ**" ማለት የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚከታተል እና የሚቆጣጠር አግባብነት ባለው ሕግ ሥልጣን የተሰጠው በባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው አካል የተመደበ ሰው ወይም የፖሊስ አባል ነው።

9) "**ተቆጣጠሪ አካል**" ማለት ይህ መመሪያ ሲጣስ ወይም የትግበራ ደረጃውን ለመከታታል ቁጥጥር የሚያደርግ በሕጋዊ መንገድ በባለስልጣኑ ወይም አግባብነት ባለው አካል ወይም በትራፊክ ፖሊስ ወይም በማህበ ወይም በድርጅቱ የተመደበ ባለሙያ ነው።

10) "**ማህበር ወይም ድርጅት**" ማለት የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ ባለንብረቶች ወይም ኦፕሬተሮች የሚያቋቁሙት ማኅበር ወይም ድርጅት ነው።

11) "**የማህበር ፈቃድ**"ማለት በማኅበር ተደራጅተው የንግድ የተሽከርካሪ ኪራይና ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ለወሰዱ ባለሀብቶች የሚሰጥ የማኅበር ምዝገባ ፈቃድ ነው።



የትራንስፖርት ባለስልጣን
አዲስ አበባ

12) **"የድርጅት ፈቃድ "** ማለትየንግድ ቢሮ ወይም የንግድ ሚኒስቴር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰዱ የንግድ የተሽከርካሪ ኪራይ የአክስዮን ማህበር፣ የግል እና ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወይም ኩባንያ ለሚያቋቁሙት ድርጅት የሚሰጥ ፈቃድ ነዉ።

13) **"ኪራይ"** ማለት ለሰዉ እና ለጭነት (ዕቃዎች) ማጓጓዥያነት የሚዉሉ ተሽከርካሪዎችን የማከራየት አገልግሎት ማለት ነው።

14) **"የንግድ ተሽከርካሪ ኪራይ ትራንስፖርት አገልግሎት"** ማለት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወስደዉ የመቀመጫ ልካቸው ከ4 ሰው በላይ ወይም ድርብ ተግባር አገልግሎት የሚሰጡ እና የጭነቱ ልክ ከ10 ኩንታል በላይ የሚጭኑ የጭነት ተሽከርካሪዎችን በማከራየት አገልግሎት መስጠት ማለት ነው።

15) **"የንግድ ተሽከርካሪ"** ማለት በንግድ ህግ መሠረት የተቋቋመ ወይም በማህበር የተደራጀ ሆኖ በአገር አቀፍ ደረጃ ባለሥልጣኑ ያወጣውን ስታዳርድ አሟልቶ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የወሰደ እና በተሽከርካሪ አከራይነት የኪራይ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ተሽከርካሪ ነው።

16) **<<ድርብ ተግባር>>** ማለት ዕቃና መንገደኞችን ለማመላለስ የተሰራ ተብሎ አግባብነት ባለው አካል የተመድበ ተሽከርካሪ ነው ።

17) **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

## 3. ዓላማ

1) በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ዉስጥ የተሽከርካሪ አከራይ አገልግሎት አሠጣጡን በአግባቡ ለመምራት እና ለመቆጣጠር እንዲቻል፣
2) በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ውጤታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ግልጽ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የንግድ የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት አሰጣጡ ምቹቱና ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ እንዲሆን ለማድረግ፣
3) የተገልጋዩን ኅብረተሰብ የመክፈል አቅም ያገናዘበ እና ያለውን ፍላጎት ለማጣጣም በፌዴራልና በሁሉም ክልሎች ሊተገበር የሚችል ሥርዓት እንዲኖር ለማድረግ፣



የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

4) በአገር አቀፍ ደረጃ ያለውን ውስን የንግድ የመንገድ የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት አቅርቦት በማሳደግ በጤናማ የገበያ ውድድር ላይ የተመሠረተ የአገልግሎት አሰጣጥ እንዲኖር ለማድረግ፣
5) በዘርፉ የተሰማሩትን ባለሃብቶች ወደ አገልግሎቱ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ሥርዓት ለመፍጠርና ለማስቻል፣
6) የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪ የኪራይ አገልግሎት አሰጣጡን በብቃት ለመምራት፣ ለመቆጣጠር እና ለመደገፍ የሚያስችል ዘመናዊ አሠራርን ሥርዓት ለማስፋፋትና ለማሳደግ ናቸው።

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በፌደራል ደረጃ ተመዝግቦ የንግድ ተሽከርካሪ የኪራይ አገልግሎት በሚሰጥ ማንኛውም ግለሰብ፣ ማህበር እና ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## በንግድ የመንገድ ማመላለሻ የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫና አደረጃጀት፤

**5. በንግድ የመንገድ ማመላልሻ ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ስለ መስጠት፡**

1) ከባለሥልጣን መ/ቤቱ በንግድ የመንገድ ማመላለሻነት የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ለመስጠት ያወጣውን መስፈርት ሲያሟሉ፣
2) በዘርፉ የተሰማሩ ወይም የሚሠማሩ አካላት አስፈላጊውን የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት ፣ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ ሲያቀርቡ፣
3) አገር አቀፍ የንግድ ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ላይ በአሽከርካሪነት የሚቀጠሩ ሠራተኞች ተገቢው የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ አግባብነት ካለው አካል የወሰዱ መሆናቸዉን ማስረጃ አያይዘው ሲያቀርቡ፤
4) ለአገልግሎት የሚያቀርቧቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት እና ሁኔታ ዝርዝር በተሰማሩበት የተሽከርካሪ ኪራይ አይነት በሕዝብና በጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ለመስራት ከማመልከቻ ጋር አያይዘው ጥያቄ ሲያቀርቡ፣

5) ቢያንስ 60 አባላትን ያቀፈ የፀደቀ የመመስረቻ ጽሑፋቸውንና መተዳደሪያ ደንባቸውን ሰነዶችን የማረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል አረጋግጠው ሲያቀርቡ እና
6) አደራጅ አካሉ ያወጣውን መስፈርት አሟልተው ሲገኙ፤

የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጣቸዋል።

6. **በንግድ ተሽከርካሪ የኪራይ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እና ለመሰማራት ሊሟላ የሚገባ መስፈርት**

**1) የተቋሙ የቢሮ እና የቦታ ሁኔታን በተመለከተ**

አገልግሎቱን ለመሥጠት በቂ እና በአግባቡ የተደራጀ ቢሮ፣ የተሽከርካሪ መቆሚያ ፓርኪንግ እና የተሽከርካሪ መጠገኛ ቦታ ያለዉ ሲሆን ባለስልጣኑ በሚያወጣዉ መስፈርት የሚፈፀም ይሆናል።

**2) በተሽከርካሪ ላይ የሚለጠፍ አርማ**

ሀ.የማህበሩን ወይም የድርጅቱን ስም እና አድራሻ የሚገልፅ ስቲከር ደረጃዉን በጠበቀ ሁኔታ በተሽከርካሪዎች ላይ በቀኝ እና በግራ በኩል መለጠፍ ያለበት ሲሆን ባለስልጣኑ በሚያወጣዉ መስፈርት መሠረት የሚፈፀም ሆኖ ማኀበሩ ወይም ድርጅቱ ለምዝገባ ሲቀርብ የስቲከሩን ናሙና ይዞ መቅረብ ይኖርበታል።

ለ.ማንኛዉም ተሽከርካሪ የኪራይ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ የሚሰማራ በንግድ የተመዘገበ መሆን አለበት።

**3) አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች የትምህርትና የሥራ ልምድን በተመለከተ**

ሀ) **ለሥራ አስኪያጅ፡**-የመጀመሪያ ዲግሪና ከዚያ በላይ የሆነ እና በማኔጅመንት፣ በቢዝነስ አድምንስትሬሽን፣ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ ትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ ኦቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ፣ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ፣በትራንስፖርት ፕላንግእና በተመሣሣይ የትምህርት ዓይነት የተመረቀ/ች እና አግባብነት ያለዉ 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለዉ/ያላት

ለ) **ለኦፕሬሽንኃላፊ፡**-የመጀመሪያ ዲግሪ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በማናጅመንት፣ ኦቶሞቲቭ ኢንጂነሪንግ፣ ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ፣ በሎጅስትክ፣ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣



የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ
የሪከርድ ... ማህደር አገልግሎት

በትራንስፖርት ፕላኒንግ እና በተመሣሣይ የትምህርት ዓይነት የተመረቀ/ች 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለዉ/ያላት።

**ሐ) ለመረጃና ትራፊክ ደኅንነት፡-የመጀመሪያ ዲግሪበትራንስፖርት ማኔጅመንት ፣** በስታስቲክስ፣ በኢኮኖሚክስ እና በIT የተመረቀ/ችእና በሞያው 2 ዓመት አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ ያለው

**መ) ለሰው ኃይል አስተዳደር፡-የመጀመሪያ ዲግሪ** በሰው ኃይል አስተዳደር፣ በማኔጅመንትወይም በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የተመረቀ/ች እና በሞያው 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ ያላት

**ሠ) ለገንዘብና ንብረት አስተዳደር፡-የመጀመሪያ ዲግሪ** በማኔጅመንት፣ በቢዝነስ ማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግ ፣በሰፕላይ ማኔጅመንትእና በተመሣሣይ የትምህርት ዓይነት የተመረቀ/ች በሞያዉ 2 ዓመት የሰራ

**ረ) ቴክኒሻን፤-** የመጀመሪያ ድግሪ በአውቶሞቲቭ፣ በመካኒካል ኢንጂነሪንግ እና በተመሳሳይ የትምህርት መስክ የተመረቀ/ች፤ በመካኒክነት ሙያ ቢያንስ 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ ያላት እና ህጋዊ የተሽከርካሪ የማሽከርከሪያ መንጃ /ፍቃድ በደረጃው ያለው ወይም ያላት፤

**ሰ) አሽከርካሪ፤-** የትምህርት ደረጃው 10ኛ ክፍል የሆነ እና በያዘው የማሽከርከር የሙያ ብቃት ደረጃ እና አይነት ቢያንስ 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው /ያላት።

## ክፍል ሦስት

## የተለዩ አካላት ተግባር እና ግዴታ

### 7.የባለስልጣኑ ተግባርና ኃላፊነት

1) በየዓመቱ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እና የተሽከርካሪው አመታዊ የቴክኒክ ብቃት ያረጋገጠበት ሠርተፍኬት ተያይዞ ሲቀርብ የምዝገባ ፈቃድ ያድሳል፣
2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የምዝገባ ፈቃዱን ያላሳደሰ ማህበር ወይም ድርጅት አገልግሎት መስጠት አይችልም፣



የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ
የሰርቶ ማህበር አገልግሎት

3) የተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት የክፍያ ታሪፍ በተጠቃሚው እና በማህብሩ ወይም በድርጅቱ መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚሠራ ሲሆን ያልተገባ የብቸኝነት አገልግሎት ለመስጠት የሚደረግ ውድድር በገበያው ውስጥ ሲከሰት ወይም አዝማሚያ ሲታይ ባለሥልጣኑ ገበያውን ማረጋጋት እና የተጠቃሚውን ፍላጎት ማረጋገጥ እንደሚገባው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥናት በማድረግ መነሻ ታሪፍ ሊያወጣ እና ሌሎች አሰራሮችና አደረጃጀቶችን ለፈጥር ይችላል።
4) ማንኛዉም አባል የኪራይ አገልግሎት ለመስጠት ወደ ሌላ ማህበር ውስጥ ለመደራጅት ቢፈለግ ከዚህ በፊት የኪራይ አገልግሎት ከሚሰጥበት ማህበር ሕጋዊ መሸኛ ደብዳቤ (Clearance) ሲያቀርብ ዝውውሩን ይፈቅዳል፣
5) ከሚመለከታቸው አካላት ወይም ማኅበር ወይም ድርጅት ጋር በመነጋገር በመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ሊያሠማራ ይችላል።
6) ባለስልጣኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝዉ የተሽከርካሪ አከራዮችን ደረጃ እና አይነት ያወጣል።
7) የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ አፈፃፀም የባለስልጣን መ/ቤቱ ሶስት ባለሙያዎች እና የብቃት ማረጋገጫ እንዲሰጠው የጠየቀው ኃላፊ ወይም ህጋዊ ወኪል በተገኙበት በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት ቼክ ሊስት መሰረት በጋራ በመሆን የሚመዘን እና ውጤት የሚሰጥ ይሆናል።
8) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 መሠረት በተሰጠው ውጤት ቅሬታ ያለው ሰው ባለስልጣኑ ባስቀመጠው የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት መሠረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።
9) እንዳስፈላጊነቱም ለተመዘገበ ማኅበር ወይም ድርጅት ካስመዘገበው ተሽከርካሪ ውጪ እንዲያሠማራ ልዩ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።

## 8. የኪራይ ተሽከርካሪ ማኀበር ወይም ድርጅት ኃላፊነት

ማንኛውም የኪራይ ተሽከርካሪ ማኀበር ወይም ድርጅት፡-

1) የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሰነድ ቅጂ አገልግሎት በሚሰጥበት ተሽከርካሪ ውስጥ ማስቀመጥና በተቆጣጣሪ አካላት ሲጠየቅም የማሳየት፤



የትራንስፖርት ... አዲስ ... የሰርቪስ ማህበሩ አገልግሎት

2) ቀጥሮ ለሚያሠራቸው ሠራተኞች የሙያና የሥነ-ምግባር ሥልጠና የመስጠት፣ መታወቂያ፣ የደረት ባጅ፣ የደንብ ልብስ እንዲያደርጉ የማድረግ፤
3) የንግድ የመንገድ ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ፈቃድ ሳይወስድ አገልግሎት አለመስጠት፤
4) በማህበሩ ወይም በድርጅቱ የሚሰጥ የመውጫ ሰነድ ሳይዝ አገልግሎት አለመስጠት፤
5) የኦፕሬተሩ ፍቃድ የሚቀየር ከሆነ ሥራ ከማቆሙ በፊት ከ15 ቀን በፊት የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ለሰጠው አካላት የማሳወቅ፤
6) በስራ ላይ እያለ በተሽከርካሪው ቴክኒክ ምክንያት ተሽከርካሪው ከቆመ ከአሽከርካሪው በተሰጠው መረጃ መሰረት ወዲያውኑ ምትክ ተሽከርካሪ መመደብ፤
7) የተሽከርካሪ የቴክኒክ ሁኔታ በዚህ መመሪያና በሌላም ሕግ ከተቀመጠው መስፈርት ውጪ ሲሆን አግባብነት ላለው አካል የማሳወቅ፤
8) ከባለሥልጣኑ በልዩ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ከተፈቀደለት የተሽከርካሪ ዝርዝርና ብዛት ውጭ አለማሳተፍ፤
9) ደህንነቱ እና ምቾቱ የተጠበቀ ተሽከርካሪ የማቅረብ፤
10) ለአገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች የወቅቱን ሙሉ ኢንሹራንስ ያላቸው መሆኑን አረጋግጦ የማቅረብ፤
11) የሚቀጥረዉ አሽከርካሪ ቀደም ሲል በትራፊክ አደጋ ያለውን ሪከርድ የሚያስረዳ የፖሊስ ማስረጃ የማያያዝ፤
12) የንግድ ትራንስፖርት ኪራይ አገልግሎት ለመስጠት የፍቃድ ጥያቄ ሲያቀርብ የሰዉ ኃይል፣ የቢሮ አደረጃጀት እና መሟላት የሚገቡ ሌሎች ሰነዶች መሟላቱን የማረጋገጥ፤
13) የራሱ የሆነ መለያ ስምና ዓርማ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ የማዋል፤
14) በአደረጃጀቱ ውስጥ የሴፍቲ ዩኒት የማቋቋም ፣
15) ጥራት ያለው የኪራይ አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ የመስጠት፤
16) ተገልጋዩ ለሚከፍላቸው ክፍያዎች ህጋዊ ደረሰኝ አዘጋጅቶ የመሥጠት እና
17) ተገልጋዩ ያለበትን ግዴታና መብቱን የማሳወቅ

ግዴታ አለበት።

9. የተከራይ ግዴታ

**ማንኛውም የኪራይ ተሽከርካሪ ለመጠቀም የተከራየ ሰው፡-**

1) ከአገልግሎት ሰጪ አካል ጋር ውል የመዋዋል፣ በውሉም መሰረት ክፍያ የመፈፀም፤
2) አገልግሎቱን ሲጠቀም ወይም ተሽከርካሪን ይዞ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ በተቆጣጣሪ አካላት ማስረጃ ሲጠየቅ የማሳየት፤
3) የተከራየዉ ተሽከርካሪ ከተበላሸ ወይም ችግር ካጋጠመው ወዲያውኑ ለማህበሩ ወይም ለድርጅቱ የማሳወቅ እና
4) በውሉ መሰረት የአገልግሎት ጊዜው ሲጠናቀቅ ተሽከርካሪውን በአግባቡ በነበረበት ሁኔታ የማስረከብ፤

ግዴታ አለበት።

10. የተቆጣጣሪው ግዴታ

**ማንኛውም ተቆጣጣሪ፡-**

1) ለቁጥጥር ሲሰማራ ራሱን የሚገልፅ መታወቂያ የማሳየት፤
2) በመንገድ ላይ ለኪራይ አገልግሎት የዋለ ተሽከርካሪን ለቁጥጥር አመቺ የሆነ ቦታዎች በመምረጥና በማስቆም ተገቢውን መረጃ የመጠየቅና የመቆጣጠር፤
3) በቁጥጥር ሂደት ጥፋት ተፈፅሞ ከተገኘ ወዲያውኑ የክስ ወረቀት በመሙላት ዋናውን ለተከሳሹ አስፈርሞ የመስጠት ወይም የቅጣት ገንዘብ የመሰብሰብ ስልጣን የተሰጠው ከሆነ የጥፋቱን አይነትና እርከን መሰረት በማድረግ የቅጣቱን ክፍያ በመቀበል ደረሰኝ የመስጠት፤
4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሰበሰበውን ገንዘብ ለሚመለከተው የስራ ክፍል የማስረከብ እና የሥራ ሪፖርት የማቅረብ እና
5) በቁጥጥር ወቅት ህጋዊ ማስረጃዎች ሳይዝ አገልግሎት ሲሠጥ የተገኘን ሰው ተሽከርካሪውን በማስቆምና በህግ ፊት በማቅረብ በወንጀል ህጉ መሠረት እንዲቀጣ የማድረግ

ግዴታ አለበት።



የትራንስፖርት ባለሥልጣን
አዲስ አበባ

# ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 11. የተከለከሉ ተግባራት

ማንኛውም የንግድ ተሽከርካሪ የኪራይ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሠጥ ድርጅት ወይም ማኅበር፡-

1. በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው አገልግሎት መስጠት፣
2. ፈቃዱን ለዕይታ በሚያመች መልኩ አስቀምጦ አለመገኘት ወይም በተቆጣጣሪ አካል ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፤
3. ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት ተሟልተዋል በሚል ያሳያቸው መመዘኛዎችን በቁጥጥር ወቅት አሟልቶ አለመገኘት፤
4. የስብሰባ ጥሪ ተደርጐለት ወይም እንዲደርሰው ተደርጐ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት፤
5. አግባብነት ካለው አካል ካልተፈቀደ በስተቀር ተሽከርካሪዎችን ከተፈቀደለት የአገልግሎት ዓይነት ውጭ እንዲሠማሩ ማድረግ ወይም በመደበኛ የትራንስፖርት አገልግሎት ላይ መገኘት፤
6. በዚህ መመሪያ የወጣውን መመዘኛ ያላሟሉ እና በተለያዩ የዲሲፒሊን ጉድለት የታገዱ አሽከርካሪዎችን መቅጠር
7. ተገቢውን የጉዞ ሠነድ አሟልቶ አለመያዝ፤
8. አገልግሎት በመስጠት ላይ እያለ በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሠረት ስቲከር አርማ በተሽከርካሪው ላይ ለጥፎ አለመገኘት፤
9. በሥራ ላይ እያለ በቁጥጥር ሠራተኞች ወይም ሌሎች ሕጋዊ አካላት ማንኛውም ዓይነት መረጃ ሲጠየቅ ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፤
10. የሚያቀርባቸዉ አሽከርካሪዎች በጉዞ ላይ የተለያዩ አደንዛዥ እፆችን እና አልኮል መጠጦችን መጠቀም፤
11. በዉል በተቀመጠው የጉዞ ኘሮግራም መሠረት ተግባራዊ አለማድረግ፤

12. ከኪራይ ዉል ስምምነት ውጪ ተጠቃሚን ማንገላታት፣ የማንጓጠጥ እና ሌሎች ኢ-ሰባዊ ተግባር መፈፀም እና፣
13. በንግድ ትራንስፖርት ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት መስጠት ስራ በኦፕሬተሮች መካከል የሚደረግ ማንኛውም ውድድር ብቸኛ አቅራቢነት ለመፍጠር እንቅስቃሴ ማድረግ፤

የተከለከሉ እና ቅጣት የሚያስከትሉ ተግባራት ናቸው፡፡

## 12. ቅጣት

በሌላ ሕግ የተከለከሉና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 የተደነገጉ ድንጋጌዎችን ጥሶ የተገኘ ማንኛውም ማኅበር ወይም ድርጅት አግባብነት ባላቸው የትራንስፖርት ሕጎችና በወንጀል ሕግ ይቀጣሉ፡፡

## 13. መመሪያውን የማሻሻል ወይም የመሻር ሥልጣን

1) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ መመሪያውን ሊያሻሽለው ይችላል፡፡
2) አግባብነት ያላቸው አካላት ይህንን መመሪያ መሠረት በማድረግ እንደ ክልላቸው ወይም ከተማቸው ነባራዊ ሁኔታ ለሚያደራጁት ማኅበር ወይም ድርጅት መመሪያ ሊያወጡ እና ይህንን መመሪያ በሙሉም ሆነ በከፊል ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

## 14.አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1) በተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት አሠጣጥ፣ በተሽከርካሪው ብቃት ጉድለት ወይም በአሽከርካሪው የህግ ጥሰትበሚያጋጥም ጊዜ ማስተካከያ እንዲደረግ እና እንደ ጉድለቱና ጥፋቱ መጠን ተቆጣጣሪ ያቃል ማስጠንቀቂያ ወይም የቅጣት ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡
2) ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ1 ላይ በተገለፀው መሠረት ጉድለቱ በተከራዩ ላይ ወይም በአሽከርካሪው ደህንነት ላይ አደጋ የማያደርስ ከሆነና በቀላሉ የሚስተካከል ሆኖ ከተገኘ ጉድለቱ ከታየበት ጊዜ አንስቶ በ48 (አርባ ስምንት) ሠዓት እንዲስተካከል እያንዳንዱ ጉድለት ተገልፆ ፁሑፍ ማስጠንቀቂያ ለንግድ ተሽከርካሪ አከራይ ማህበር ወይም ድርጅት ወይም ለአሽከርካሪው ይሰጣል፡፡



የትራንስፖርት ባለሥልጣን የሬከርድና ማህደር አገልግሎት

3) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ2 ላይ በተገለፀው መሠረት ጉድለቱ በተከራዩ ላይ ወይም በአሽከርካሪዉ ደህንነት ላይ አደጋ የሚያደርስ ሆኖ ከተገኘ ተቆጣጣሪው ተሽከርካሪው አገልግሎት መስጠቱን እንዲያቆም አድርጎ ከ14 (አስራ አራት) ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲስተካከል እያንዳንዱ ጉድለት ተገልፆ አስተካክሎ አገልግሎት ለመስጠት ብቁ መሆኑን እንዲያሳውቅ የቅጣት ማስጠንቀቂያ ለማህበር ወይም ድርጅት ወይም ለአሽከርካሪው ይሰጣል።
4) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ የተገለፁትን ማስጠንቀቂያ ሳይተገብር አገልግሎት ሲሰጥ የተገኘ ማህበር ወይም ድርጅት ወይም አሽከርካሪ እንደጉድለቱና ጥፋቱ ክብደት ተቆጣጣሪው በሚያቀርበው ሪፖርት አግባብነት ያለው አካል የኦፕሬተር ፍቃዳቸውን ሊያግድ ወይም ሊሰርዝ ይችላል።

## 15. አባሪ ሰነዶች

ከዚህ መመሪያ አተገባበር ጋር በተያያዘ ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው መስፈርቶች እና የሚያስተላልፋቸው የደብዳቤ ልውውጦች የዚህ መመሪያ አባሪ ሰነዶች የሆናሉ።

## 16. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ---መጋቢት 11--- ቀን ---2011--- ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አብዲሳ ያደታ

የትራንስፖርት ባለስልጣን

ዋና ዳይሬክተር